# ምድብ አራት (ከ7ኛ — 9ኛ) ክፍል
## 21 ኛ ሳምንት
## የጠፋው ልጅ

**ዓላማ**

- የእግዚአብሔርን ፍቅር መማር

**የሚጠና ጥቅስ**

- ***"ጠፍቶ ነበር ተገኘ "*** ሉቃ. 15÷24

**ምንባብ**

- ሉቃ 15

**መግቢያ**

- በዛሬው ትምህርታችን ለመዝናናትና ነጻነት ብሎ ከአባቱ ቤት ስለኮበለለ ወጣት እንማራለን፡፡

**ትምህርቱ**

- ሁለት ልጆች የነበሩት ሀብታም ሰው ነበር፡፡ አንድ ቀን ታናሽ ልጁ ***"ከገንዘብህ የሚደርሰኝን ስጠኝ"*** አለው፡፡ አባቱ ከሰጠው በኋላም ሩቅ አገር ሄዶ በከንቱ አባከነውም፡፡ ብዙ ጓደኞችን ያዘ፡፡ በሂደትም ገንዘቡን ጨረሰ፡፡
- ገንዘቡ ሲያልቅም ለሚበላው ምግብ ልመና ጀመረ÷ ነገር ግን ገንዘብም ሆነ ሥራ አላገኘም፡፡
- በኋላም አሳማ አርቢ አሳማዎችን ሊጠብቅለት ቀጠረው፡፡ ከመራቡም የተነሣ የአሳማ ምግብ ሊበላ ይመኝ ነበር፡፡
- አሳማዎቹ ሲበሉ አይቶም፣ ***"እንጀራ የሚተርፋቸው የአባቴ ሙያተኞች ስንት ናቸው? እኔ ግን ከዚህ በራብ እጠፋለሁ፡፡ተነሥቼም ወደ አባቴ እሄዳለሁና÷አባቴ ሆይ÷ በሰማይና በፊትህ በደልሁ ወደፊትም ልጅህ ልባል አይገባኝም ከሞያተኞችህ እንደ አንዱ አድርገኝ እለዋለሁ፡፡"*** ብሎ አሰበ፡፡
- ከረጅሙ ጉዞ በኋላም አባቱ ቤት ደረሰ፡፡ አባቱ ከሩቅ አይቶትም÷ ከጠፋበት ቀን ጀምሮ ይጠብቀው ነበርና አቅፎ ሳመው ***"እነሆ ይህ ልጄ ጠፍቶ ነበር ተገኝቶአል"*** አለ፡፡
- ልጁም ***"ልጅህ ልባል አይገባኝም ከባሮችህ እንደ አንዱ ቁጠረኝ"*** አለው፡፡
- አባቱ ግን ሳይቆጣ በፍቅርና በይቅርታ አገልጋዮቹን ***"ፈጥናችሁ ከሁሉ የተሻለ ልብስ አምጡና አልብሱት፣ ለእጁ ቀለበት ለእግሩም ጫማ ስጡ፤ የሰባውንም ፍሪዳ አምጥታችሁ እረዱለት÷ እንብላም ደስም ይበለን፤ ይህ ልጄ ሞቶ ነበርና ሕያው ሆኖአል፤ ጠፍቶም ነበር ተገኝቶአልም ::"*** ደስም አላቸው፡፡

**ማጠቃለያ**

- የጠፋው ልጅ ÷አባካኝ ልጅ ነበር፡፡ ከቤተሰቡ ገንዘብን ወስዶ ያጠፋውም ለዚህ ነበር፡፡ ስህተቱ ከአባቱ ቤት መኮብለሉ ብቻ ሳይሆን ገንዘቡን ማባከኑና ግዴለሽነቱም ነበር፡፡
- ሁላችንም ስህተት እንሰራለን ይህ አባት የልጁን መመለስ ይጠባበቅ እንደነበረም÷ ስንመለስ እግዚአብሔር መመለሳችንን ይጠብቃልና - ይቅር ይለናል፡፡
- ነገር ግን እኛ ኃጢአታችንን በማመን እንደጠፋው ልጅ ***"በድያለሁ"*** ብለን ለካህናት መናዘዝም ይገባናል፡፡
- የእግዚአብሔር ቃል ***"በአንድ ኃጢአተኛ መመለስ በእግዚአብሔር መላእክት ፊት ደስታ ይሆናል፡፡"*** ሉቃ.15÷10 ያለውም ለዚህ ነው፡፡

**ጥያቄዎች**

1.ትንሹ ልጅ የአባቱን ቤት ትቶ ለመሄድ ለምን ፈለገ?

2. አዲሶቹ ጓደኞቹስ እስከመጨረሻ ከርሱ ጋር ኖሩ፡፡

3. የጠፋው ልጅ ገንዘቡን ሲጨርስ ምን ዓይነት ሥራ ውስጥ ገባ?

4. ወደ አባቱ ቤት ለመመለስ ለምን ወሰነ?

5. ሲመለስ ለአባቱ ምን አለ?

6. ልጁ ሲጸጸትና ሲመለስ አባቱ ምን አለው?

7. እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን ይጠላል? ስንመለስስ ምን ይላል?

8. ይህ ታሪክ የት ይገኛል፣ ማን ተረከው? መጽሐፉንስ ማን ጻፈው?

**ይቆየን፡፡**